የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን

ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

July 10, 2026
Addis Ababa, Ethiopia

# Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) Grants Licenses to Three New Capital Market Service Providers

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) is proud to announce the granting of licenses to three (3) new capital market service providers (CMSPs) after a rigorous license application review process. In addition, the ECMA has approved the licensing of ten (10) Appointed Representatives and the appointment of fifteen (15) board directors of the three newly licensed service providers.

The Director General of the ECMA, Hana Tehelku, formally presented the license to the leadership of the three newly licensed service providers during licensing event took place on Friday, 10 July 2026, at the ECMA's Head Office; increasing the total number of licensed CMSPs from eighteen (18) to twenty-one (21), total number of Investment Banks to eight (8) and total number of Securities Investment Advisors to eleven (11).

The new licensees and their license categories are:

**1. PrizeWorth Investment Bank S.C - Investment Bank**

**2. BluFin Capital Advisory PLC – Securities Investment Advisor**

**3. Lumina Capital PLC - Securities Investment Advisor**

During the licensing event, the Director General of the ECMA, Hana Tehelku, extended her congratulations to the newly licensed service providers. The Director General urged the new licensees to deliver market-expected services with expertise and integrity, maintain investor inclusion approach, and remain consistently dedicated to public interest.

The ECMA extends its congratulations to the three newly licensed service providers and reaffirms its commitment to a strong inclusive, and resilient capital market in Ethiopia.

**For enquiries & additional information contact**

Contact: Communications & Public Relations Directorate

Phone: 011 557 81 19

Email: communication@ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

ሐምሌ 3፣ 2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለሦስት አዲስ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ ሰጠ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ከሰፊ የፈቃድ ማመልከቻ ግምገማ ሂደት በኋላ ለሦስት (3) አዳዲስ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፍቃድ በመስጠቱ የተሰማውን ደስታ ይገልጻል።

በተጨማሪም ባለስልጣኑ የሦስቱን አዳዲስ አገልግሎት ሰጭዎች አስር (10) ተሿሚ እንደራሴዎችን ፈቃድ ያጸደቀ ሲሆን፣ የ አስራ አምስት (15) ቦርድ አባላት ሹመትንም አጽድቋል።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል ሃና ተኸልቁ ፈቃዱን ሐምሌ 3 ቀን 2018 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤት በተዘጋጀ መርሃ ግብር ለሦስቱ አዳዲስ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች አመራሮች በይፋ ያስረከቡ ሲሆን፣ በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ጠቅላላ ቁጥር ከአስራ ስምንት (18) ወደ ሀያ አንድ (21)፣ ከፍ ሲል፤ የኢንቨስትመንት ባንኮች ቁጥር ወደ ስምንት (8) እና የሰነደ ሙዓለንዋዮች የኢንቨስትመንት አማካሪዎች ቁጥርም ወደ አስራ አንድ (11) ከፍ ብሏል።

አዳዲሶቹ ፈቃድ የተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች እና የፈቃድ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡

1. **ፕራይዝዎርዝ ኢንቨስትመንት ባንክ አ.ማ- በኢንቨስትመንት ባንክ ዘርፍ**

2. **ብሉፊን ካፒታል አድቫይዘሪ ኃ.የተ.የግ.ማ- በሰነደ ሙዓለንዋይ ኢንቨስትመንት ማማከር ዘርፍ**

3. **ሉሚና ካፒታል ኃ.የተ.የግ.ማ- በሰነደ ሙዓለንዋይ ኢንቨስትመንት ማማከር ዘርፍ**

በፈቃድ አሰጣጥ መርሃ ግብሩ ላይ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ጀነራል ሀና ተኸልቁ በዕለቱ ፈቃድ ለተሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፤ ገበያው ከአገልግሎት ሰጭዎች የሚጠብቀውን አገልግሎት በዕውቀት፣ በታማኝነት እና ሁሉንም ኢንቨስተሮች ባማከለ መንገድ አገልግሎታቸውን መስጠት እንዳለባቸው እና በማንኛውም ጊዜ ለህዝብ ጥቅም በቁርጠኝነት እንዲሰሩ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን በኢትዮጵያ ጠንካራ እና አካታች የካፒታል ገበያ ስርዓት እንዲገነባ ያለውን ቁርጠኝነት እየገለጸ አዲስ ፈቃድ ለተሰጣቸው ሦስቱ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ይወዳል።

---

## ለጥያቄዎችና ተጨማሪ መረጃ

**የኮሙኒኬሽን እና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**
**ስልክ: 011 557 81 19**
**ኢሜይል: communication@ecma.gov.et**